በሲያትል ሕግ መሠረት ስለ

# አድልዎ ስለተሞላበት ጥቃት

ማወቅ ያለብዎ

አድልዎ የተሞላበት ጥቃት ወይም ዐመፅ ሲባል የሲቪል መብትዎን የሚጥስ እና በዘርዎ፣ በሐይማኖትዎ፣ በፆታዎ እና/ወይም የፆታ አመለካከትዎ፣ ያለብዎ አካል ጉዳተኝነት፣ ዜግነትዎ፣ እና ሌሎች ምክንያት የሚደርስብዎ ነው። የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦ **ማስፈራራት፣ ማዋረድ ወይም ቅፅል ስም ማውጣት፣ የማስፈራሪያ ማስጠንቀቂያ መስጠት ወይም ማስገደድ፣ ዐመፅ ወይም ሐይል መጠቀም፣ ንብረትን ማጥፋት ወይም ማበላሸት እና በኢንተርኔት አማካኝነት ማስፈራራት።**

- **ሲያትል ውስጥ አድልዎ የተሞላበት ጥቃት ሕገ ወጥ ነው።**
- ቤት ውስጥ፣ ሥራ ቦታ፣ ወይም ብሕዝብ ቦታ ላይም ቢሆን **ማንኛውንም ሰው ከአድልዎ የተሞላበት ጥቃት የተጠበቀ ነው።**
- **አድልዎ የተሞላበት ጥቃትን ሪፖርት ማድረግ ቀላል ነው።** ሂደቱን ለመጀመር ወደ Seattle Office of Civil Rights (SOCR፣ ሲያትል ከተማ የሲቪል መብት ቢሮ) ይደውሉ።
- **ሪፖርት ሲያደርጉ ማንነትዎ በሚስጢር ሊያዝ ይችላል።**
- SOCR **አድልዎ የተሞላበት ጥቃትን ለማስቆም ሊረዳ ይችላል።**
- **አካላዊ ዐመፅ፣ ንብረት ማውደም ወይም ማስፈራት የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን የሚጥስ እና ወደ 911 ፖሊስ ጋር በቀጥታ በመደወል ሪፖርት ማድረግ ይቻላል።**

SOCR *እርስዎን በቤትዎ ውስጥ፣ በሥራ ቦታዎ፣ እና ሕዝብ በሚጠቀምበት ቦታዎች ላይ* ከአድልዎ የተሞላበት ጥቃት ለመጠበቅ የቆመ ነው። Seattle Police Department (SPD፣ የሲያትል ፖሊስ ቢሮ) ከከፍተኛ ጥቃት የሚጠብቅዎት ሕግ ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ከወንጀል ጎራ የማይመደቡትን ሌሎች የአድልዎ ተግባራትን መዝግቦ ይይዛል።

ወደ SOCR ብለው ወደ **206.233.7100** በመደወል ስላጋጠመው አድልዎ የተሞላበት ጥቃት ሪፖርት ያድርጉ።

በአድልዎ ስለተደረገ ወንጀል ወደ **911** ወደ ፖሊስ በመደወል ሪፖርት ያድርጉ።

Seattle
Office for Civil Rights

http://www.seattle.gov/civilrights

http://www.seattle.gov/police/safety/harassment/